# ጥላሁን ህያው ነህ!

(ከግርማ ላቀው ታምሬ)

ኤፕሪል 22/2009--ኤድመንተን፤ ካናዳ

## የጥላሁን ገሠሠ ዕረፍት ለማክበር

### በኤድመንተን ኢትዮጵያዊያን ኅብረተ-ሰብ ማኅበር
### ዝግጅት ላይ ለማቅረብ የተጠናቀረ።

ያኔ ያኔ ገና ከልጅነትህ --- በመረዋው ድምፅህ
ሁሉን አስደስተህ -- ወጣት--ጎልማሶችን
አሩግ--ህፃናትን

ከሰሜን--ከደቡብ -- ከምስራቅ--ከምዕራብ
መላ ኢትዮጵያዊውን፤
ጠኔ ሲበረታ--ርሃብ ሲስሉ...
የፍቅር አንጀትህ አላስችል ቢልህ
አልቅሰህ አስለቀስህ...
ለወገኖችህ ታደግህ፤
ስቆ የሚያስቅ አልቅሶ የሚያስለቅስ አሉህ
ጥላሁን ከፍ አልህ --- ኩራት የወገኖችህ
ተመሰከረ--የኪነት ሰው--ሙሉዕነትህ።

የፍቅር ቡራኬህን--ለሚዋደዱ ፍቅረኞች፤
የፍቅር መልዕክትህን--ለተራራቁ ጎልማሶች፤

የሀገር ፍቅርህን ለጦር ሜዳ ጀግኖች፤
በመረዋው ድምፅህ--ስታጽናና...
ስታክም ስታድናቸው፤
ስትደግፍ--አይዞን ስትላቸው፤
ዶክተር ጥላሁን አሉህ ቢበዛ ፍቅራቸው፤

እና ጥላሁን--የዘመኑ ወረርሽኝ--ጉንፋን፤
ይህ ክፉ ምች... ሀበሻ ሲያርመሰምስ---ብዙውን

ከአብሮነት ይልቅ መለያየት በአደባባይ ሲወደስ
ሳይበግርህ... ተጠይፈህ--አጠገብህ ሳታስደርስ፤

ከዚህ አቲካራ ከፍ ብለህ--በፍቅር ሀኪምነትህ
...በዓለም አቀፋዊ ሰብአዊነትህ፤
ለክፍፍል--ሳትጠቃ--ሳትንበረከክ፤
የዚህኛው የዚያኛው--የጥፋት አሽኮለሌ፤
ሳያደናቅፍህ--ቀጠልህ--የአንድነትን ምሳሌ

በመረዋ ድምፅህ ሁሉን እያስደሰትህ፤

ለብዙ ዓመታት የፍቅር ሰባኪነትህ እንደበራ፤
ሸንተረር ሜዳውን--ገደሉን--አቋርጦ ተራራ...
መዋደድን እያወደስህ፤
አንድነትን እያደነቅህ፤
ለሀገር ተቆርቋሪነትህ --መሪ ኮከብ ሚና ተጫወትህ፤
ዘመናዊው ኋላ ቀርነት ሳያታልልህ፤

ለሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች፤
የአንድነት--የፍቅር--ዜማዎች፤
ስትጫወት--በሁሉም ልብ ስትነግሥ
ታላቅ ሀኪምነትህ ሲፈውስ፤
የሙዚቃው አባት የሚዚቃው ንጉሥ
ዶክተር ጥላሁን ቢሉህ አዎ ሲያን ነው ሲያንስ።

እንዴ ቋሚ እኮ ነው....የኛ ጀግና ሥራህ፤
የሁል-ዓቀፍ የሠላም--የፍቅር መንፈስህ፤
ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ድምፅህ፤

እስኪ ማን ነው?--ባንት ፈዋሽ ድምፅ ያልዳነ፤
ባንተ ጡኡመ ዜማ ያልተፅናና--ያላመነ?
በዘፈንህ አጋዥርንት -- ፍቅሩን--በትዝታ ያላዋደደ
ታላቁን መፍትሔ የፍቅር ዘፈንህን ያላስተናገደ?
ማን ነው የፍቅርን መዛባት የመውደድን መሳከር በሽታ፤
ያላስታመመ--ባንተው ሙዚቃ...ቀንም ሆነ ማታ?
ባንተው ድምፅ ያልተዝናና ወይም ያልተሸነፈ ያልተረታ?

ታዲያ ይህ ግዙፍ ቋሚ ሥራህ--ህያው ስለሆነ...
ከአጠገባችን ብትለይ--በአካል ብትሞትም፥
ህያው ነህ እንጂ ጥላሁን.... ሞትህ'ኮ አይባልም።

የኢትዮጵያ ንብረት ነህና የሁላችን፤
ተቀርፀሃልና በልብ ውስጥ--በህዝባችን።
ህያው ነህ ጥላሁን... ደስ ይበልህ ደስ ይበለን